**ደብዳቤ ለወላጆች - ወደ መደበኛው**

ውድ ወላጆች፤

ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ በእስራኤል መንግስት እንደተወሰነው እንዲሁም በጤና ሚኒስቴር ቁጥጥር እና ሂደት መሰረት መዋለህፃናት ቀስ በቀስ ወደ ስራ ይመለሳሉ፡፡ ይሄ የመመለስ ሁኔታ ለወላጆች ወደ ስራ ለመመለስ እና በዚህ በውስብስብ ቀውስ ግዜ ውስጥ ለሚገኘው የእስራኤል ኢኮኖሚ አስዋፅኦ ለማድረግ እንድትችሉ ይረዳችኋል፡፡

በመማር ማስተማር ውስጥ ካሉት ችግሮች በተጨማሪ ይሄ የመመለስ ሁኔታ የጤና ችግር ለሁላችንም አለው፡ ፡ ልጆች ወደ መዋለህፃናት ሲመለሱ በመጀመሪያው ደረጃ ሁሉንም ጓደኞቻቸውን እንደማያገኙ እና ስሜታቸውን እና ስጋቶቻቸውን መወያየት እንዳለባቸው እንዲያውቁ ማዘጋጀት ይመከራል፡፡ ጓደኞቻቸውን፣ አስተማሪዎቻቸውን እና ሌሎቹንም በመናፈቃቸው የሚሰማቸውን ስሜታቸውን ማስተላለፍ የሚችሉበትን መንገድ ይስጡአቸው፡፡

የኢንፌክሽን እና የተላላፊ በሽታን ለመከላከል የመዋለህፃናቱ መምህራን እና እናንተ ወላጆች የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል ወሳኝ ነው፡፡

የመደበኛ የመዋለ ህፃናት ተግባራት ለመጠበቅ የሚከተሉትን ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡

- ልጆች ከ 38 ዲግሪ ሴልሽስ በላይ ሙቀት እንደሌለው እና በአሁኑ የበሽታ ምልክቶች እንዳልታመመ የሚያሳይ ‘የጤና መግለጫውን’ ፎርም መፈረም ይጠበቅቦታል። በየጠዋቱ ይህንን ፎርም ማምጣት አለቦት። ይህንን ፎርም ሳይፈርም የመጣ ወላጅ ልጁን ወደ መዋለህፃናቱ ማስገባ አይችልም፡፡

<u>በተገቢው ቋንቋ የተዘጋጀውን ‘የጤና መግለጫውን’ ለማግኘት የሚያስችለውን ማስፈንጠሪያ ያስገቡ</u>

- ህፃናቱ የራሳቸውን ቁርስ ይዘው ይመጣሉ (ምግቦች በመዋለህፃናቱ አይቀርብም)። ሁሉም ህፃናት የራሳቸውን ቁርስ በሳጥን ማምጣት እና ምግብ ሲበሉ ጠረጴዛው ላይ የሚያደርጉት ናብኪን ይዘው መምጣት አለባቸው፡፡ ጤነኛ ሳንዱዊች ከተቆረጠ እና ለመብላት ከተዘጋጀ አትክልት እና የተቆራረጠ ፍራፍሬ ጋር ማምጣትን እንመክራለን፡፡
- ማንኛውም የመፀዳዳት ተግባር ወይም ማንኛውም ተግባር ከመደረጉ በፊት እና በዋላ የግል ንፅህና መጠበቅ በትክክል መደረግ አለበት፡፡ ሰራተኞች እና የመዋለህፃናቱ ልጆች እጃቸውን በሳሙና እና በውሃ መታጠባቸውን ያረጋግጣሉ፡
- ልጆችን ወደ መዋለህፃናቱ ጠዋት ማምጣት እና ከትምህርት በሁዋላ መውሰድ አለበት፡፡
- የህፃናቱ ወደ ትምህርት ተቋም መግባት እና መውጣት በመዋለህፃናቱ መምህር ወይም በረዳቱ/ቷ ይደረጋል፤ ይህ ሲሆን በግልፅ ቦታ ላይ የሚገኝ ሁሉም ሰው የፊት መሸፈኛ እና የግል ርቀት መጠበቁ ተረጋግጦ ነው፡፡
- በተገኙት ሁሉ መሃል የ2-ሜትር ርቀት መጠበቅ አለበት፡፡
- ወደ መዋለህፃናቱ የእርሶን መግባት እና ውስጥ መገኘት አንፈቅድም፡፡

እንደ መዋለህፃናቱ የመያዝ አቅም መዋለህፃናቱ ለሁለት ወይም ለሶስት ቡድን ይከፈላሉ፡፡ ስለ ቋሚ ሰራተኖች የጤና ሚኒስቴት ውሳኔ መሰረት እያንዳንዱ ቡድን እስከ 15 ልጆች ያካትታል፡፡

መዋለህፃናቱ ክፍት የሚሆነው ከ 8፡00ኤኤም እስከ 2፡00 ፒኤም ድረስ ነው፡፡

ተጨማሪ ጥያቄዎትን በሚመለከት፤ የመዋለህፃናቱ ቡድን ከእርሶ ለሚነሱ ማንኛውም ጉዳዮችን ለመፍታት ይገኛል፡፡

በፍጥነት ወደ ድሮው ጤናማ ቀናት እንደምንመለስ ከተስፋ ጋር፤ ስለ ትብብሮት እናመሰግናለን።